# የወንጌል መልዕክት

በቄስ ካዋንካ ሱ አ

እኔ ማን ነኝ? ከየት ነው የመጣሁት ወዴት ነው የምሄደው? ሁሉም ሰዎች በዕድሜያቸው ቢያንስ አንድ ጊዜ ይህን ጥያቄ ራሳቸውን ይጠይቃሉ። የሚጠይቁበትም ምክንያት እውነተኛ ሰላምና ደስታ ወደ ሕይወታቸው ማምጣት ስለሚፈልጉ ነው። የሰው ልጆች በራሳቸው ጥረት መፍትሄ ለማግኘት ይፈልጋሉ፡ ይጠይቃሉ ብዙ ይለፋሉ። ነገር ግን ይህ በእንዲህ እንዳለ ሕይወታችን ቀጣይነት ባለው ችግርና መከራ ውስጥ ሁልጊዜ ትቀጥላለች። አንዳንድ ጊዜ ልንገምተው ከምንችለው በላይ የሆነ ክስተት በሕይወታችን ውስጥ ይከሰትና በራሳችን ሀይል መፍትሄ ማምጣት አንችልም።

እንዳጋጣሚ ሆኖ ከላይ ከተገለጸው ችግርና መከራ አንዱ በሕይወትህ ያውቃል?

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| የመጀመሪያ ግንኙነት | |
| ሰዎች ለምንድነው በሕይወታቸው ደስተኛ የማይሆኑት? | 3 |
| ሁለተኛ ግንኙነት | |
| ሰዎች ለምንድነው እግዚአብሔርን መገናኘት የማይችሉት? | 5 |
| ሦስተኛ ግንኙነት | |
| እንዴት እግዚአብሔርን መገናኘት ትችላለህ? | 7 |
| አራተኛ ግንኙነት | |
| ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ኢየሱስ ብቸኛ መንገድ የሆነው ለምንድነው? | 9 |
| አምስተኛ ግንኙነት | |
| ለምንድነው ማረጋገጫ የሌለን? | 11 |
| ስድስተኛ ግንኙነት | |
| አሁን ድኛለሁ፡ ስለዚህ እንዴት ነው የተለወጥኩት? | 13 |
| ሰባተኛ ግንኙነት | |
| ከዚህ በኋላ እንዴት ነው መመላለስ ያለብህ? | 15 |
| ስምንተኛ ግንኙነት | |
| መቼ ነው የእግዚአብሔር ሀይል የሚገለጸው? | 17 |
| ዘጠነኛ ግንኙነት | |
| ጸሎት መንፈሳዊ ምርምር (ሳይንስ) ነው | 19 |
| አሥረኛ ግንኙነት | |
| በሽታችን (ህመማችን) ስንጸልይ የሚለቀን ለምንድነው? | 21 |

# 1

## ሰዎች ደስተኛ የማይሆኑት ለምንድነው?

ሁሉም ኃጢአት ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋልና (ሮሜ 3፡23)

ሰዎች ደስተኛ መሆን ሲገባቸው ለምንድነው ደስተኛ የማይሆኑት? በተቆራኛቸው በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ይኖራሉ። እነርሱም የቤተሰብ ችግር፣ የጤና ችግር የገንዘብ ችግር፣ወደፊት ምን ይፈጠራል በማለት የመጨነቅ ችግር የመሳሰሉት ናቸው። ይህንም ስሜት ለመርሳት መጠጥ በመጠጣት፣ ቁማር በመጫወት፣ በመደነስ ወይም በመጨፈር ወይም የመኖር ተስፋቸውን በማጣት የጠለቀ ተስፋ ቢስነት ውስጥ ይገባሉ። ለዚህ ሁሉ ችግር ምክንያቱ ምንድነው?

### 1. ምክንያቱም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ተለያይተዋል።

1. ለእግዚአብሔር መታዘዝ ባለመፈለግ እግዚአብሔርን ትተዋል (ዮሐ 10፡10 ሮሜ 3፡23)
2. በዚህም ምክንያት በኃጢአት ዓለም ገብተዋል (ሮሜ 3፡10)።
3. በሁሉመ አይነት መከራ ወስጥ ወድቀዋል።
   1) የአእምሮ ችግር አለባቸው (ማቴ 11፡28)
   2) ለክብራቸው የማይገባና ያልተመጠነ ኑሮ ይኖራሉ (ማቴ 12፡25)
   3) በአካላዊ በሽታ ይሰቃያሉ (ሐዋ 8፡7-8 ማቴ 8፡16-17)
   4) መሠረታዊ ችግር - መንፈሳዊ ችግር
4. መፍትሄ ለማግኘት ፊታቸውን ወደ አስማተኞችና ጠቋንዮች ወይንም ወደተለያዩ ኃይማኖቶች ያዞራሉ።

### 2. የሰዎች ደስተኛ ያለመሆን መቼ እንደጀመረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

1. ደስተኛ ያለመሆን የጀመረው በመጀመሪያው የሰው ልጅ አባት እና እናት በሆኑት አዳምና ሔዋን ነው።
2. መሰረታዊ ምክንያቱ (ዘፍ 3፡1-15)፣ ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዝዘ ኃጢአት መሥራት።
3. ውጤቱ (ዘፍ 3፡16-19)፣ በመከራና በእርግማን ወስጥ መግባት።

### 3. ይህ ደስተኛ ያለመሆን መቼ ያበቃል?

1. አሁንም እንደቀጠለ ነው (ኤፌ 2፡1-2)
2. ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል (ማቴ 11፡28-29)
3. ችግሩን ለመፍታት ብንጥርም እየከፋ ይሄደል (ማቴ 12፡43-45)

### 4. ደስተኛ ያለመሆን ችግር የማይወገደው ለምንድነው?

1. ደስተኛ እንዳንሆን የሚያደርገን አንድ አካል አለ።
2. ስሙም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል

1) ሰይጣን 2) ዲያቢሎስ 3) እርኩስ መንፈስ

3. መቼ ነው እርሱ የተገለጠው?
    1) የእግዚአብሔር መልአክ በኃጢአት ወደቀ ከሰማይም ተጣለ (ሕዝ 28፡14-19)
    2) ከሰማይ ወደ አየር ላይ ተጣለ (ኤፌ 2፡2)።
    3) በምድር ላይ እየዞረ የሰዎችን ሕይወት ያበላሻል ያጠፋልም።
    4) በመጨረሻም ወደ ሲዖል (የዘለዓለም እሳት) ይጣላል (ማቴ 25፡41)።

## 5. እግዚአብሔርን ባለማወቅ ብትቀጥል ምን ይከሰታል?

1. መንፈሳዊ ችግር ይመጣል (ዮሐ 8፡44)።
2. ምክንያቱን ባላወቅከው ብዙ ችግር ወስጥ ትገባለህ (ሐዋ 10፡38፣ 8፡7-8) ።
3. ደስታ አይኖርህም (ማቴ 12፡25-28)።
4. በልብህ ውስጥ ሰላም የለህም (ማቴ 11፡28)።
5. አካላዊ በሽታ ያሰቃይሃል (ሐዋ 8፡4-8)።
6. በአዕምሮአዊ ችግር ትሰቃያለህ (ሐዋ 16፡16-18)።
7. መጨረሻህም የዘለዓለም እሳት ይሆናል (ሉቃ 16፡19-13)።

## 6. በዚህ ምድር ሰዎች የሰጡን ሰላም ጊዜያዊ ነው

1. ምድራዊ ሰላም ነው።
2. የአጭር ጊዜ ደስታ ነው።
3. ለጊዜያዊ ደስታ ብቻ ይጠቅማል።
4. በመጨረሻም ታላቅ ሀዘን ይፈጥራል።

- **ጥንቆላ፡ ዕድል ነጋሪነትና መተተኝነት (ትናንሾቹን መናፍስት በማባረር የበለጠ ሀይል ያላቸው መናፍስትን መቀበል)**

1. እነዚህን ነገሮች ለረጅም ጊዜ መለማመድ በሕይወታችን ውድቀትን ያስከትላል።
2. ዘለዓለማዊ ነጻነት የምናገኝበት መንገድ
    1) የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል ባለመታዘዛቸው ምክንያት በሀጢአት የመውደቃቸውን እውነታ ተረዳ (የሰው ልጆች መሠረታዊ ችግር፡ ዘፍጥረት 3)
    2) በክርስቶስ ኢየሱስ እመን እርሱንም የግል አዳኝህ አድርገህ ተቀበል (ዮሐ 1፡12)
    3) ከእግዚአብሔር ጋር የመሆን ሥልጣን ይኖርሃል (ማቴ 28፡20)

# 2

## ለምንድነው ሰዎች እግዚአብሔርን መገናኘት የማይችሉት?

ድነት በሌላ በማንም አይገኝም፡ እንድንበት ዘንድ ለሰዎች የተሰጠ ከዚህ ስም በስተቀር ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለምና። (ሐዋ 4፡12)

ሰዎች ከእግዚአብሔር ስለተለዩ ደስታ ቢሶች ናቸው። ከእግዚአብሔር የተለየ ሕይወት በመቅበዝበዝ የተሞላ ነው። ታዲያ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የማይችሉት ለምንድነው?

1. **ምክንያቱም ሰዎች ከእግዚአብሔር ስለተለዩ ነው።**
    1. መንፈሳቸው ሙት ነው (ኤፌ 2፡1)
    2. ያሉት የእግዚአብሔር መንፈስ ከእነርሱ በተለየበት ሁኔታ ነው።
        1) የመጀመሪያው ሰው- የእግዚአብሔር መንፈስ ከሰው ጋር ነበር (ዘፍ 1፡27)
        2) ከውድቀት በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ሲለይ መንፈሱ ሙት ሆነ። ስለዚህም ያልተቋረጠ የደም መስዋዕት ካላቀረበ ሰው ወዲያውኑ መርገምን ይቀበላል (ቃየን)።
        3) የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ስለተለየ የሰይጣን መንፈስ ገብቶ ተቆጣጠረው (1ቆሮ 2፡12)።
    3. እውቀታቸውና ሀሳባቸው ጭምር ስለጨለመ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ችል ብለዋል (2ተሰ 2፡10-11)።
    4. የእግዚአብሔርን ቃል ቢቀበሉም ሊረዱት አልቻሉም (2ቆሮ 4፡4-5)።

2. **ሰዎች እግዚአብሔርን ለመገናኘት እየታገሉ ነው።**
    1. የሰው ዘር መንፈሳዊ ፍጥረት ነው፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን የመፈለግ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ በውስጣችን አለ።
    2. ሰዎች ሐቀኛ በመሆን እግዚአብሔርን መገናኘት እንደሚችሉ ያስባሉ ያ ግን መጨረሻው ውድቀት ነው።

3. ሰዎች ኃይማኖት መልስ እንደሆነ ያስባሉ ስለዚህም ይማኖተኛ ለመሆንና ኃይማኖታዊ ሕይወትን በቅንዓት ለመኖር ይጥራሉ (ማቴ 12፡43-45)
4. ሰዎች በፍልስፍና እግዚአብሔርን ለመገናኘት ይሞክራሉ ነገር ግን ስላልቻሉ ወደከፋ ባዶነት ውስጥ ይገባሉ (ቆላ 2፡8-9)

3. **ደህንነትን ካላገኘህ ከእግዚአብሔር ጋር ልትገናኝ አትችልም**
   1. ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት በመጀመሪያ ደህንነትን ልታገኝ ይገባል።
   2. ዳግመኛ ሳትወለድ እግዚአብሔርን ልታየው አትችልም (ዮሐ 3፡3-5)
   3. ደህንነት ማለት ከሰይጣን፣ ከዕድልና ከዕጣ ፈንታ ነጻ መሆን ማለት ነው።
   4. ደህንነት ማለት ከኃጢአት ወስጥ መውጣት ማለት ነው።
   5. ደህንነት ማለት ከሲያል ኃይል ማምለጥ ማለት ነው።
   6. ሲያል ለሰይጣንና ለመላዕክቱ የተዘጋጀ ቦታ ነው (ማቴ 25፡41)
   7. መንግስተ ሰማይ ለእግዚአብሔር ልጆች የተዘጋጀ ቦታ ነው።

4. **ሙታን መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ሁሉ የሙት ነፍስ ጥረትም እንዲሁ ዋጋ የለውም**
   1. ደህንነትን ያላገኙ ሰዎች ጥረት የሚያስገኘው ውጫዊ ለውጦችን ብቻ ነው።
   2. እነዚህ ጥረቶች መልካም ቢሆኑም ደህንነትን ግን አያስገኙም።
   3. በምድር ላይ መንግስተ ሰማያትን ለማስገኘት ብቃት ያለው ምንም ነገር የለም።

5. **በሥራህ (በጥረትህ) ደህንነት ለማግኘት የማትችለው ለምንድነው?**
   1. መንፈስህን በራስህ ጥረት ልትዋጀው አትችልም።
   2. በሌሎችም እርዳታ መንፈስህን ልትዋጀው አትችልም።
   3. ሰይጣንን ለማሸነፍ ወደምድር የተላከ ማንም ጀግና የለም (ሐዋ 4፡12)።
   4. ደህንነት የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (ኤፌ 2፡8-9)

- ፈውስ - መጥፎ ህልሞች
  1. የጤና ችግሮች - ያልተቃረጠ ስፖርት፡ ሥርዓት ያለው ሕይወት፡ አመጋገብ
  2. የጽሞና ጸሎት - ጽሞና
  3. የታቀደ ጸሎት - ዳን 6፡10,22 ዘፍ 13፡18 ሐዋ 3፡1 ሐዋ 16፡16-13

# 3

## እንዴት እግዚአብሔርን መገናኘት ትችላለህ?

ኢየሱስም እንዲህ አለው «መንገዱ እኔ ነኝ፣ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐ 14፡6)

1. **እግዚአብሔር መንፈስ ነው**
    1. እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በስጋዊ ዓይንህ ልታየው አትችልም።
    2. ስለዚህ እግዚአብሔር በምንም ወይም በማንም አይወሰንም። በሰዋዊ እጅ የተሠራ ማንኛውም ነገር አምላክ አይደለም። ያ ጣዖት ስለሆነ አጋንንት በውስጡ ያድራሉ (1ቆሮ 10፡20)
    3. እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ በሁሉም ቦታ ይገኛል።
    4. እርሱ ሁሉን አዋቂ ነው።
    5. እርሱ ሁሉን ቻይ ነው።
    6. ስለዚህም ያህዌ ተብሎ ይጠራል።
    7. እኛም መንፈሳዊ ፍጥረቶች ስለሆንን ደህንነት ማለት መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር መገናኘት ማለት ነው (ኢሳ 40፡18-31)።

2. **ነገር ግን አንተ ሥጋዊ አካል ነው ያለህ**
    1. እግዚአብሔርን ልታየው አትችልም።
    2. መንፈስህ በሥጋዊ አካልህ ውስንነት ይገታል።
    3. መንፈስ ከሥጋዊ አካልህ ሲለይ ሞት ይባላል።
    4. የደህንነት ዕድል የሚኖርህ በሥጋዊ አካልህ እስካለህ ድረስ ብቻ ነው (ሉቃ 16፡19-31)።

3. **እግዚአብሔርን የመገናኛ መንገድ**
    1. ሰውን ለማዳን መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር በሰው አምሳል መጣ (ዮሐ 1፡14)።
    2. ስለዚህም እርሱ ኃጢአት የለሽ ነው የእርሱ መንፈስም የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።
    3. እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
    4. ኢየሱስ መለኮታዊና ሰብዓዊ ተፈጥሮ አለው (ማቴ 16፡16-19)
        1) መሲህ (ክርስቶስ) - አዳኝ፣ አምላክ
        2) የእግዚአብሔር ልጅ - ሥጋ ለብሶ መጣ

5. ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል እግዚአብሔርን የምንገኛኝበት መንገድ ነው (ዮሐ 1፡12 ራዕ 3፡20)።
6. ኢየሱስ ክርስቶስን ስትቀበል መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ ሊያድር ወዳንተ ይመጣል። ደህንነት ማለት ያ ነው (ዮሐ 14፡15, 26-27)።
7. በዚህ ጊዜ የሰይጣን ኃይል ሙሉ በሙሉ ካንተ ይርቃል።
8. እስቲ ኢየሱስን ለመቀበል ከልባችን እንጸልይ።

**4. እግዚአብሔር ካንተ ጋር የመሆኑ ማረጋገጫ**

1. መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ ሊያድር ሲመጣ ሊመራህና በየቀኑ የቅድስናን ጎዳና ሊያሳይህ ይጀምራል። (ዮሐ 14፡26-27)
2. የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ስትቀበል መንፈስ ቅዱስ ይመራሃል።
    1) መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዕብ 4፡12)።
    2) ቃሉን ስትቀበል መንፈስህ ይነቃቃል (መዝ 119፡25)።
3. ኃጢአትህ መፍትሄ ሲያገኝ መንፈስ ቅዱስ ይመራሃል (መዝ 66፡18 ገላ 5፡16-18)።
4. ከልብህና በትጋት በተወሰኑ የጸሎት ርዕሶች ላይ መጸለይ ስትጀምር የእግዚአብሔርን ኃይል ትለማመዳለህ።
5. ባንተ ላይ መብትን ያጣው ሰይጣን በአጋንንቱ አማካኝነት ሊያሰናክልህ ይሞክራል። ለዚህም ነው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ የነገረን (ኤፌ 5፡18)።
6. በመንፈስ ቅዱስ ስትሞላ ኃይል ይሰጥሃል (ሐዋ 1፡8)።
    1) ራስህን
    2) ዓለምን
    3) ሰይጣንን ልታሸንፍ ትችላለህ
7. የወንጌል በር ይከፈታል።
8. የእግዚአብሔር ሕያውነት ማረጋገጫዎች ይገለጣሉ።
9. ዮሐ 14፡6ን ልትረዳ ትችላለህ።

- ፈውስ - ጭንቀት
    1. ቃሉ፡ የሕይወት ውሀ (ሕዝ 37፡1-10)
    2. የማያቋርጥ የጸሎት መንገድና ኃይል

# 4

## ኢየሱስ ለኛ ብቸኛ መንገድ የሆነው ለምንድነው?

ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያቢሎስ ነው:: ምክንያቱም ዲያቢሎስ ከመጀመሪያ አንስቶ ኃጢአት ስለሚያደርግ ነው:: የእግዚአብሔር ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ነው::(1 ዮሐ 3፡8-10)።

1. ብዙ ሰዎች ደህንነትን ዝም ብሎ ከመኖር መለየት አይችሉም
   1. ሁሉም ኃይማኖቶች አንድ እንደሆኑ ያስባሉ::
   2. የሁሉም ኃይማኖቶች ግብ መልካም ሥራን መሥራት እንደሆነ ያስባሉ::
   3. ለመዳን  መንገዱ መልካምና በጎ ምግባራትን መፈጸም እንደሆነ ያስባሉ::
   4. ክርስትና ኃይማኖት ሳይሆን በራሱ ሕይወት ነው::
   5. ኃይማኖት የተፈጠረው በሰው ሲሆን ወንጌል ግን የተሰጠው በእግዚአብሔር ነው::
   6. ኃይማኖት ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚያደርገው ፍለጋ ሲሆን ወንጌል ደግሞ እግዚአብሔር ሰውን ፍለጋ እንደመጣ የሚነግረን መልዕክት ነው::
   7. የኃይማኖት ማነጻጸሪያው የሰው ሥራ ሲሆን የወንጌል ማነጻጸሪያው የእግዚአብሔር የደህንነት ሥጦታ ነው::

2. ብዙ ሰዎች ያልዳኑ ሰዎች የሚኖሩበትን የኩነኔ ሕይወት አያስተውሉም፤፤
   1. የመጀመሪያው ኃጢአት ያልዳኑ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ያጎላል(1 ዮሐ 3፡8-10)።
   2. ይህ ማለት እነርሱ ሁላቸውም በዘፍጥረት ምዕራፍ 3(ኤፌ 2፡2-3) በተገለጠው ሰይጣን እጅ ውስጥ ናቸው ማለት ነው::
   3. የኩነኔ ሕይወት አስፈሪ ነው::
      1. ይህ መንፈሳችን በሰይጣን መንፈስ ቁጥጥር ስር የሚሆንበት ሕይወት ነው::
      2. መንፈሳችን በእርግማን ስር የሚሆንበት ሕይወት ነው::
      3. በተለምዶ እነዚህ ሰዎች የመጨረሻ ጥፋታቸው እስከሚመጣ ድረስ በጣዖት አምልኮ፣ በቅድመ አያቶች አምልኮ፣ በድግምት፣ በጥንቆላ፣ በመተት፣ በአስማተኞችና በባዕድ አምልኮዎች ይሰቃያሉ::
         - ሀ.ሕይወታቸው ውድቀትን እንደተሞላ ይህቺን ምድር ለቀው ይሄዳሉ።
         - ለ.ጥፋት እስከ  ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ደረስ ይቀጥላል። (ዘጸ 20፡4)
         - ሐ.ሥጋዊ አካሎቻቸው በአእምሮ በሽታ፣ በአጋንንታዊ በሽታ እና ምክንያቱ በማይታወቅ በሽታ ይሰቃያሉ። (ማቴ 8፡16-17)

4.በመጨረሻም የሕይወታቸው መቋጫ በሲያል ይሆናል። (ሉቃ 16፡19-31፣ ራዕ 14፡1-9)

3. **አንድ አዳኝ ብቻ አለ።**
    1. ሰይጣንን ለማሸነፍ ኃይል ያለው እርሱ ብቻ መሆን አለበት።
    2. ሥጋ ለብሶ መምጣት ነበረበት (ዮሐ 1፡1፣ 14)
    3. ኃጢአት የለሽ መሆን ነበረበት (ዕብ 4፡15፣ 1 ጴጥ 3፡18)
    4. ከአዳም ዝርያ መሆን አልነበረበትም (ከድንግል ነው የተወለደው)
    5. የኃጢአትን ዋጋ ለመክፈል ኃጢአት የለሽ ሰው መሞት ነበረበት (ዘፍ 2፡17)
    6. አምላክነቱን ለማረጋገጥ ከሞት መነሣት ነበረበት (1 ቆሮ 15፡3-5)።
    7. ይህ ሰው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም።
    8. እርሱ ራሱ አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የሰይጣንን ኃይል ማሸነፍና ሰውን ማዳን የሚችለው (ፊል 2፡6-9)።
    9. ይህ ዛሬም የተረጋገጠ እውነት ነው (ሐዋ 16፡16-18)

4. **ደህንነት በትክክል ምንድነው (ኤፌ 2፡1-6)**
    1. አጥፊ ወጤቶች ካሉት ኃጢአት ነጻ መውጣት ነው።
        1. የውርስ ኃጢአት = ዘለዓለማዊ ኩነኔን የሚያመጣ ኃጢአት (ኤፌ 2፡1)
        2. እውነተኛ ኃጢአቶች - ከውርስ ኃጢአት የሚመጡ ኃጢአቶች (ኤፌ 2፡1)
        3. የአባቶች ኃጢአቶች - የአባቶች በዘራቸው ላይ ውድቀትን የሚያመጡ የጣዖት አምልኮ ኃጢአቶች (ዘጸ 20፡4)
    2. ከሰይጣን ኃይልና ከመጨረሻ ዕድል ፈንታው ማምለጥ ነው (ኤፌ 2፡2)።
    3. ወደፊት በመንግስተ ሰማያት መቀመጥ ነው (ኤፌ 2፡6)።
    4. የዚህ ማረጋገጫው በአሁኑ ሕይወታችን ይገለጣል (ኤፌ 2፡7)

- ፈውስ - በአጋንንታዊ ተጽዕኖ ለሚሰቀዩ

    1. እምነት ዘፍ 3፡15፣ ማቴ 16፡13-15፣ 17፡1-8፣ 28፡16-20፣ ሐዋ 1፡8
    2. መንፈሳዊ ኃይል - የታቀደ ጸሎት፣ የማያቋርጥ ጸሎት፣ መንፈሳዊ ኃይል
- እስቲ 1ዮሐ 3፡8 ን ለመረዳት እንሞክር

# 5

## ዋስትና የሌለው ለምንድነው?

*ምስክርነቱም ይህ ነው፡ እግዚአብሔር የዘለዓለምን ሕይወት ሰጠን፡ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው። ልጅ ያለው ሕይወት አለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። (1 ዮሐ 5፡11-13)*

ብዙ ቤተክርስቲያናት ስለመዳን (ደህንነት) ምንም አይነት ዋስትና የለም ይላሉ በግልፅ። ብዙ አማኞች አሉ ስለደህንነታቸው (ስለመዳናቸው) እርግጠኞች ያልሆኑና ነገር ግን ይህን አምነው የማይቀበሉ። በተጨማሪም ሌሎች ሰዎች አሉ ይህንን ለማረጋገጥ የተለያዩ የሞኝነት ሥራ የሚሰሩና ራሳቸውን ለዚህ ተግባር የሰጡ ምክንያቱም ምንም ዋስትና የላቸውም።

ለምንድነው ያለዋስትና መኖር የቀጠሉት? ለዚህ ጥያቄ የግድ መልስ ማግኘት አለብን።

1. **ምክንያቱም በክርስቶስ በማመን አዲስን ሕይወት ያገኙ ሰዎችን ሕይወት ስለማያውቁ**
   1) የዳነ ሰው ማለት በእርግጠኝነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በፍጹም ልቡ በፍጹም ሐሳቡ አምኖ የተቀበለና ሀጢአቱን የተናዘዘ ማለት ነው (1ኛ ዮሐ 1፡12 ራዕ 3፡20)
   2) ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ በተቀበለ ሰው ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ይሠራል በራሳቸው ሀይል አይኖሩም። ይህ እውነት ነው (ሮሜ 8፡2፣ 1ቆሮ 3፡16፣ 12፡3)
   3) ይህ አዲስ ሕይወት (መንፈስ ቅዱስ) የሌለው ሰው ሁኔታ ምን ይመስላል
      1. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር በሀጢአት ምክንያት ከተለያዩ በሃላ የሚኖሩትን አሮጌውን ሕይወት ይኖራል።
      2. መንፈሱን ሰይጣን ይቆጣጠራል (ዮሐ 8፡44፣ ሐዋ 10፡38)
      3. ብዙ ነገር ሊኖረው ይችላል ነገር ግን ሰላም የለውም (ማቴ 11፡28-29)
      4. ስኬታማ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ችግር አይለየውም (ማቴ 12፡25)
      5. ሰውነቱ በሰይጣን ቁጥጥር ስር ይሆናል፡ በሰይጣን ይመራል። ምንም ነገር ያለእርሱ አያውቅም (ኤፌ 2፡2-3)
      6. ከጊዜ በሃላ ሰውነቱ (አካሉ) በሽተኛ ይሆናል (ሐዋ 8፡4-8)
      7. ልቡና አእምሮው ከሰይጣን ጋር የተገናኙ ናቸው (ሐዋ 16፡16-18)
      8. በመጨረሻም ይህቺን ዓለም ሲሰናበት ወደ ሲያል ይሄዳል። (ሉቃ 16፡19-31)

2. **ምክንያቱም በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎችን በረከት ስለማያውቁ ነው**
   1) በክርስቶስ የዳኑ ሰዎች በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣ እርግማንና ኩነኔ ነጻ ናቸው። (ኤፌ 2፡21)
      - ✓ ከአዳም ከወረሱት ኃጢአት
      - ✓ እራሳቸው ከሠሩት ኃጢአት
      - ✓ ከዘር ማንዘር ከወረሱት ኃጢአት
   2) ከዚህ ዓለምና ከሰይጣን ተጽዕኖ ነጻ ወጥተዋል (ኤፌ 2፡2)

3) ውስጣቸው ሲያልን ከመፍራት ነጻ ነው። (ኤፊ 2፡6)
4) ለሚመጣው ትውልድ ምስክርነታቸውን አኑረዋል። (ኤፊ 2፡7)

3. **ምክንያቱም በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎች ያገኙትን ጥቅም ስለማያውቁ (ማቴ 16፡13-16)**
   1) ለቅዱሳን ብቻ የተሰጠውን ወንጌልን የመስበክ (የማወጅ) ጥቅም
      1. እንደ ዓለት ጠንካራ አድርጎ ሠርቶአቸዋል (ጽናት)
      2. ቤተክርስቲያኑን መሰርታል (ወንጌል)
   2) ቅዱሳን ሰይጣንን ማሸነፍ የሚችሉበትን ሃይል የማግኘት ጥቅም ተሰጥቷቸዋል።
      1. ብዓለም ስንመላለስ ሁልጊዜ ውጊያ ውስጥ መኖራችንን አውቀን እንድንገባ የመኖረን አመለካከት (1 ጴጥ 5፡8፣ ያዕ 4፡7)
      2. እስከመጨረሻ ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን አመለካከት (ሉቃ 18፡5)
   3) ለቅዱሳን ብቻ የተሰጠ የጸሎት መልስ የማግኘት ጥቅም
      1. በረከት ይህውም ሰይጣን ላላመኑ ሰዎች የሚሰጠው በተወሰነ ኃይሉ ይህም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው። (ምሳ 16፡4)
      2. ስለዚህ የጸሎት መልስ ለማግኘት ቁልፍ ያስፈልገናል።

4. **ምክንያቱም በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎችን አኗኗር ስለማያውቁ**
   1) ያልዳኑ ሰዎችን አኗኗር ሁኔታ እንወቅ
   2) የዳኑ አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ማግኘት አለባቸው (ዮሐ 14፡26-27)
      1. ጭንቀታቸውን ማስወገድ (1 ጴጥ 5፡7)
      2. ራስህን በሙሉ ስትክድ ከዚህ በሃላ ሁሉን ነገር ልታገኝ ትችላለህ (ገላ 2፡20)
   3) በመንፈስ ቅዱስ መመራት ከፈለግህ/ሽ
      1. ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ማዕከል መሆን አለበት (2ኛ ቆሮ 5፡17)
      2. ጸሎት የመጀመሪያ ጉዳይ መሆን አለበት። (ሐዋ 16፡ 13-16)
      3. ሕይወትህ/ሽ በሙሉ ወንጌልን መስበክ አለበት። (ሐዋ 1፡8)

- ፊውስ -በዘር ለሚተላለፍ አምልኮ ችግር
  1. የሞተ ሰው ምኞት (ሉቃ 16፡19-31)
  2. የዘር አምልኮ - ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ኢ. ሳይንሳዊ፣ የረከሰ ነው
  3. ከዘር አምልኮ የሚመጣ መንፈሳዊ ችግር (1ኛ ቆሮ 10፡10፣ ማቴ 12፡13-35)

# 6

## አሁን ድኛለሁ እንዴት ነው የተቀየርኩት?

እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል። መንፈሱም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንካ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል።. . . በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በቀር በሰው መካከል የአንድን ሰው ሀሳብ የሚያውቅ ማን አለ እንደዚሁም . . . (1ኛ ቆሮ 2፡10-14)

እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ለማዳን ሁሉን ነገር በነጻ አድርጎልናል። ቃልም ሥጋ ሆነ (ዮሐ 1፡14)፣ ደሙን አፈሰሰ፣ ከሞት ተነሳ፣ ከሞት ተነሣ ወደሰማይ አረገ አሁንም ከላይ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ይመለከተናል። ሆኖም ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች መዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተረዱም።

1. ስለ *መዳናችን ያለን የተሳሳተ አመለካከት ምንድነው (ደህንነት ያልሆኑ ነገሮች)?*
    1. የተሳሳተ ሀሳብ ሀይማኖትን ድነት ያመጣ አድርገን ማሰባችን (ዮሐ 3፡1-10) ሃይማኖት በሰው ነው የተፈጠረው። ስለዚህ ወንጌል አይደለም። ምንም እንኳን መልካም ነገር በማድረግ የተመሠረተ ቢሆንም ያልዳነ ሰው መልካም ሥራ ሊያደርግ አይችልም። ቢያደርግም እንኳን መልካሙ ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ አይታወቅም (ዮሐ 3፡1-10)።
    2. ደህንነት ማለት ያለማቋረጥ ቤተክርስቲያን መሄድ (መሳተፍ) እንደሆነ ማሰብ። ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል (ማቴ 12፡43-45) እንደተናገረው በከንቱ ቤተክርስቲን መመላለስ ፍሬቢስ ሲሆን እንዲያውም ለታዳሚው ተጨማሪ ሸክም ብቻ ይሆንበታል።
    3. ጠንካራ ወይም የተሰጠ ቤተክርስቲያን አባል በመሆናቸው የዳኑ ይመስላቸዋል። የፈሪሳውያንን ቅናት ታስታውሳለህ? ቡድሂስቶችስ ጠንካራና ቀናተኛ አይደሉም? ይህ መሰጠት መጨረሻው ባዶነት እና ውድቀት (ተስፋ በመቁረጥ) ብቻ ይሆናል።
    4. በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ድነት ጠንካራ በሆነ አንድ እምነት (ፍልስፍና) የሚገኝ አድርጎ ማሰብ። ይህ አስቂኝ ነገር ነው። በእንደዚህ አይነት አሳብ የተሞሉ ብቻቸውን ሲሆኑ ብቸኝነትና ውድቀት ይሰማቸዋል።
    5. ድነት የሚገኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በማወቅ፣ ሃይማኖታዊ ቃላትን በመጠቀም እና በመጸለይ ነው ብሎ ማሰብ። እነዚህ ሁሉ ውጫዊ ለውጥ ያመጣሉ። ነገር ግን ውስጣዊ ለውጥ በፍጹም አያመጡም። በማቴ 11፡28-30 በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ወስጥ ያሉ ሰዎች ወደ እርሱ እንዲመጡ ሲጋብዝ እናያለን።

**2. ስለዚህ የዳነ ሰው ሁኔታዎች ምንድናቸው?**

1. ውስጣዊ (መንፈሳዊ) ለውጥ
2. ድነት አገኘህ ማለት መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ ያድራል (ይኖራል) ደግሞም ይገዛሀል።

3. ሮሜ 8፡2 ይህ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይናገራል። ዮሐ 3፡3-5 እውነት እልሃለሁ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም።
4. ዮሐ 14፡16-17 እንደሚናገረው መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው፡ አይተወንም አይጥለንም።
5. የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆንህን ከተረዳህ
    1. ሮሜ 8፡2፣4፣9 እንዲህ ይላል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መዳናችን ሙሉ ይሆናል የሕግ ፍጻሜ ይሆናል።
    2. የእግዚአብሔርን ፍቃድ፣ በረከት እና ጸጋ ወደ ማወቅ ትመጣለህ (1 ቆሮ 2፡10-14)።
    3. የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ መሆንን ወደማወቅ ትመጣለህ (1 ቆሮ 3፣16)።
    4. መንፈስቅዱስ በሕይወትህ ያልተስተካከለውን ነገር ያስተካክላል (ገላ 5፡16-18)።
    5. መንፈስ ቅዱስ ይመራሃል ምክንያቱም አንተ ደካማ ነህ (ዮሐ 14፡26-27)።
    6. መንፈስ ቅዱስ በሠላም ይመራሃል (ዮሐ 14፡27)።
    7. መንፈስ ቅዱስ ጸሎትን ይመልሳል (ሮሜ 8፡26)፡
    8. ሁሉንም ነገሮች ወደ መልካምነት ይቀይራል (ሮሜ 8፡28)።

**3. ወደ ድነት እንዴት ልትገባ ትችላለህ?**

1. በኢየሱስ ክርስቶስ መኖር ማለት የኢየሱስ ሕይወት ባንተ ወስጥ ሲኖር ማለት ነው።
2. ይህ ማለት ከውኃ እና ከመንፈስ (ከላይ ከሆነው) መወለድ ነው።
3. አንድ መንገድ ብቻ አለ (ዮሐ 3፡16)።

**4. የዳኑ (መንፈስ ቅዱስ የተቀበሉ) ሰዎች ሕይወት ወስጥ አራት ነገሮች ይከሰታሉ። አራት ነገሮች ይቀየራሉ።**

1. በመንፈስ የቤተሰብ ማንነታችን ይቀየራል (ዮሐ 8፡44 <—>1 ዮሐ 3፡2፣ዮሐ 5፡24)
2. ያለህበት ሁኔታ ይቀየራል (ሮሜ 6፡17 <—> ሮሜ 6፡22)
3. ያለህበት መንፈሳዊ እና ሥጋዊ ኑሮ ይቀየራል (ኤፌ 2፡1 <—> ኤፌ 2፡5)
4. የሕይወትህ ምሪት ይለወጣል (ኤፌ 2፡2 <—> ገላ 5፡18)

**5. ይህ ሕይወት ያላቸውን እግዚአብሔር እንዴት ይመራቸዋል?**

1. አይተውህም/ሽም አይጥልህም/ሽም ነገር ግን ይመራሃል እስከመጨረሻው ያነጻሃል። (ዮሐ 14፡16፣26 ገላ 5፡16-18)
2. ይህን ሕይወት ያገኙትን ማንም አያጠፋቸውም። ለማረጋገጥ ሮሜ 8፡31-39 እንደ

- ፈውስ - በሱስ አስያዥ መድሃኒት ለተያዙት

1. መንፈሳዊ ፈውስ (ሐዋ 1፡4-8፣ 1ቆሮ 2፡10፣ 1ዮሐ 2፡20-27፣ ሐዋ 1፡8)
2. አካላዊ ፈውስ (ደም፣ የደም ቧንቧ)

# 7

## ከዚህ በኋላ እንዴት መመላለስ አለብህ ?

እንግዲህ እኔ በዓለም አልቆይም . . .ዮሐ 17፡11-12

አሁን ድነሃል። የተሟላ መንፈሳዊ ነጻነት አግኝተሃል፡ ነጻ ሆነሃል። ስለዚህ ከዚህ በኋላ በምድር ስትኖር ምን ማድረግ አለብህ?

1. **በጥብቅ እወቅ(አስታውስ) ሰይጣን እስከ ዓለም መጨረሻ (የመጨረሻው ፍርድ) ድረስ ይኖራል።**
    1. የሰይጣንን ሥራ የሚገልጠው በዓለም ላይ ያለ ብቸኛ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
    2. ሰይጣን ራሱ ተቀጥቅጧል (ዘፍ 3፡15)። ሰይጣን መጨረሻው እንደቀረበ ያውቃል። ስለዚህም በተቻለው መጠን ወደሲዖል ከመሄዱ በፊት ጥፋት መከራ መፍጠር ይፈልጋል።
    3. በዚህ ዓለም መጨረሻ ሰይጣን ሥልጣኑን ያጣል (ማቴ 25፡41)
    4. ነገር ግን መከላከያህን አትለጣል። ምክንያቱም ሰይጣን ክፉ መንፈሱን መጠቀም ይጀምራል። የውሸት መንፈስ፣ የውሸት ነቢያት፣ የውሸት (የሃሰት) ትምሕርትና አጋንንት ይዋጋሃል።
    5. በየዕለቱ በጸሎት ድል አድርግ (ኤፌ 6፡18)
    6. ሰይጣን ቤተሰብህን ሊያጠፋ ይመክራል (ማቴ 12፡28-29)
    7. ሰይጣን ያላመኑ ሰዎችን ሊውጠ ይዞራል፣ እንዲሁም ያመኑ ሰዎችን ያለዋስትና ሊያስቀር ይፈልጋል (1ጴጥ 5፡7-8)
    8. አጋንንት ወደ ሕይወትህ እንዲገባና አንድ ጊዜ ከፈቀድክ ከርሱ የባሱ ሰባት አጋንንትን ጨምሮ ይመለሳል (ማቴ 12፡44-45)
    9. ሁሉንም አይነት በሽታዎችን ይፈጥራል (መድህኒት ያልተገኘላቸውና፣ ያልታወቁ በሽታዎች) ማቴ 8፡15-17
    10. ግራ መጋባትን ወደ አእምሮህ ያመጣል (ማር 5፡10፣ ሐዋ 16፡16-18)
    11. በእምነታቸው ብርቱ የሆኑ ሰዎች አጠገብ ይዞራል (ያዕ 4፡7)
    12. ሰይጣን ዕረፍት ለማግኘት ደረቅ ውኋ በሌለበት ደረቅ ቦታ ይንከራተታል (ማተ ₀12፡43-44)
    13. ሰይጣን በተለየ ሁኔታ ባዶ ቤት ለመግባት ይፈልጋል (ማቴ 12፡45)
    14. በጣም የሚጸልዩና መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቁ ቅዱሳንን በጣም ይጠላል (1 ተሰ 5፡16-18)
    15. በእውነትና በመንፈስ የሚያመልኩ ሰዎችን በጣም ይጠላል (ማቴ 4፡8-11)
    16. በእግዚአብሔር ቀን መገኘትንና ወንጌልን ይፈራል።

2. **ስለዚህ የሚከተሉትን አምስት ነገሮች አስታውስ ደግሞም ኑርባቸው።**

1. ኢየሱስ ክርስቶስን በአግባቡና በጥልቀት እወቀው (ኢሳ 53፡5፣ ዮሐ 1፡2፣ 1 ዮሐ 3፡8)። ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሙሉ በሙሉ ስልጣኑን ያጣል ወይም ይታሰራል።
2. በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ያለህን እምነት አጠንክረህ ቀጥል፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን። (ዮሐ 3፡16)
3. በጸሎት፣ በእምነት ሁልጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን የልብህ፣ የቤትህና የሁሉም የሕይወትህ ዘረፎች ማዕከል አድርገው።
4. የኢየሱስ ክርስቶስን ሥልጣንና ስም በሕይወትህ ቅድሚያ ሰጥተህ ስትቀበልና ስትመሰክር በዚያን ጊዜ ድልን ታገኛለህ። (ሮሜ 10፡9-10፣ ማቴ 10፡32-33፣ 16፡13-18፣ ሐዋ 2፡21)
5. ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትህ ጌታ ሲሆን ምንም አይነት ችሎታ፣ ሁኔታዎች፣ እውቀትና የጀርባ ታሪክ ቢኖርህም መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ መሥራት ይጀምራል።

**3. ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ተመልከትና አንተ የት እንዳለህና የት መሆን እንዳለብህ መርምር።**




የተፈጥሮ ሰው | ዓለማዊ ሰው | መንፈሣዊ ሰው

1. ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገው፣ ከዚያም ጭንቀትህን፣ ችግሮችህንና የኃጢአት ሸክምህን በእርሱ ላይ ጣል።
2. ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገው የራስህን ነገር አስወግድ።
3. ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገው ጭንቀቶችህን (አሉታዊ የሆነ አመለካከትህን) አስወግድ።
4. ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገው በራስህ እውቀትና ልምድ አትደገፍ።
5. ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ማዕከል አድርገው ከዚህ ሌላ የሚታወቅ ነገር አይኑርህ። ምክንያቱም በአንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ፍጹም ነው።

- ፈውስ - በድካም ጊዜ (የእግዚአብሔርን ኃይል የምንለማመድበት መንገድ)
  1. የታቀደ የጸሎት ጊዜ
  2. ተከታታይ ጸሎት
  3. በአንድነት መጸለይ (በሕብረት ሆኖ መጸለይ)
  4. በትኩረት (በተመስጦ) መጸለይ
  5. በመናገርና በመስማት መጸለይ
  6. በሥልጣን መጸለይ (መንፈሳዊ ሥልጣን በመጠቀም መጸለይ)

# 8

## መቼ ነው የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጸው?

ኢየሱስም ወደ እነርሱ ቀረበ . . . ማቴ 28፡18-20

1. በመጀመሪያ ሰባት ነገሮችን በአእምሮህ አኑር።
   1. ሰው በመጀመሪያ የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዲኖረው ነው። (ዘፍ 1፡27)
   2. ነገር ግን በሰይጣን ምክንያት ይህ አምሳሉ ጨልሟል። ወደ ሞት ዓለም ገብቷል። (ዘፍ 3፡1-10፣ ኤፌ 2፡1-2፣ ዮሐ 8፡44)
   3. ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ውድቀት፣ ሞት እና መከራ ያለማቋረጥ ገቡ። (ዘፍ 3፡11-20)
   4. በዚህ ዓለም የምትኖረው የእንግድነት ኑሮ ነው፣ ከዚያም ወደ ቤትህ ትመለሳለህ (ቤትህ መንግስተ ሰማያት ወይም ሲያል ሊሆን ይችላል።) (ሉቃ16፡19-31)
   5. እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም በሰው ውስጥ የተበላሸውን የእግዚአብሔር አምሳል ለማደስና የጠላትን ሥራ ለማፍረስ መጣ። (1 ዮሐ 3፡8)
   6. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርና ሰው ነው። (ዮሐ 1፡14፣ ፊል 2፡6-10)
   7. ኢየሱስ ክርስቶስን ስትቀበል ወይም ሕይወትን ስትቀበል ችግሮችህ በሙሉ መፍትሔ ያገኛሉ። (ማቴ 11፡28)

2. አሁን ሦስት ውጊያዎችን ለመዋጋት ተዘጋጅ
   1. ውጊያ ከራስህ ጋር «እውነትን ካወቅህ እውነት ነጻ ያወጣሃል።» (ዮሐ 8፡32)
      1) ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጥና እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ዘለዓለማዊ እቅድ ተረዳ።
      2) የራስህን ፈቃድ መከተል በመተው የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ፍልግ (በጌታ ጸሎት)።
      3) በራስህ ዕቅድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዕቅድ ተማመን። የእግዚአብሔር ዕቅድ ዓላማ ፍጹም ነው። (ሮሜ 8፡25)
      4) ከዚህ በኋላ  በራስህ አሳብና አስተሳሰብ መመራት አይጠቅምህም።
      5) ራስህን ሙሉ በሙሉ ለጌታ አሳልፈህ ስጥ።
      6) እውነት ኢየሱስ ነው። እርሱ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ኑሮ ነጻ ያወጣሃል።
   2. ውጊያ በመጨረሻው ጊዜ ሊያስትህ ወይም ሊያታልልህ ከሚሞክረው ከሰይጣን ጋር
      1) በራስህ ብርታት ሰይጣንን ማሸነፍ አትችልም ነገር ግን በኢየሱስ ኃይል ትችላለህ።
      2) ዮሐ 1፡12 እግዚአብሔር የሰጠንን የልጅነት «መብት» ይናገራል።
      3) ማቴ 18፡28 ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይና በምድር ሥልጣን እንዳለው ይናገራል።
      4) ሁሉም አይነት አጋንንቶች ለኢየሱስ ስልጣን ይገዛሉ። (ማር 1፡27)
      5) ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠበት ምክንያት የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ ነው። (1 ዮሐ 3፡8)
      6) ጸሎትን ሰምቶ መመለስ የእግዚአብሔር ሥልጣን ነው። (ዮሐ 16፡24)

3. ውጊያ ዓለምን በመቃወም - የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ተቀበል።
    1) ዮሐ 14፡16 በዚህ ቦታ እንደተጠቀሰው አማካሪው(መንፈስ ቅዱስ) ከአንተ ጋር ለዘለዓለም ይኖራል።
    2) በዮሐ 14፡26-27 እንደተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር ያስታውስሃል።
    3) በ 1 ዮሐ 2፡20 እንደተዘረዘረው አንተ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ተቀብለሃል ስለዘህ እውነትን ታውቃለህ።
    4) በ ማቴ 12፡28 እንደተዘረዘረው መንፈስ ቅዱስ በሚገኝበት ቦታ የእግዚአብሔር መንግሥት አለ።
    5) ሐዋ 1፡8 እንደሚናገረው ኃይልን ትቀበላለህ።

**3. የእግዚአብሔር ኃይል መሥራት የሚጀምረው መቼ ነው?**

1. የእግዚአብሔር ልጅ ወደመሆን በተመለስክ ጊዜ በረከቱ መሥራት ይጀምራል - በተፈጥሮ በወረስነው ኃጢአት ምክንያት የሚመጣ ችግር ሁሉ ይፈታል።
2. ኃጢአት ይቅር ሲባል ወይም ሲወገድ መሥራት ይጀምራል።
3. በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈልግ፡ በመከራ ወስጥ፣ በስደት ወቅት፣ በበሽታና በተስፋ መቁረጥ መካከልም ቢሆን።
4. በሕይወትህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ዓላማ ፈልግ።
5. በምትኖርበት ቦታ እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ዓለማ ፈልግ።
6. ለእነዚህ ነገሮች ስትጸልይ የእግዚአብሔር ኃይል በአንተ ላይ ይመጣል።
7. ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን በቂህ ከሆነ ድልን ትቀዳጃለህ።

ፈውስ = የአዕምሮ ጤና

1. ማቴ 12፡25-45
2. ሐዋ 16፡16-18
3. ማር 5፡1-10

# 9

## ጸሎት መንፈሣዊ ሳይንስ ነው

«እናንተ ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካምን ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ» ሉቃ 11፡5-3፣ 18፡1-8

እግዚአብሔር ኃያል አምላክ ስለሆነ ጸሎትን ይሰማል፣ ይመልሳል። ኃጢአተኛ ሆነህ ጥያቄ ይዘህ ወደ እርሱ መቅረብ አትችልም። ነገር ግን ምንም ኃጢአት ባልሰራው በኢየሱስ ስም ብትቀርብና ብትጸልይ ጸሎትህን ይመልሳል ። (ዮሐ 16፡24)

1. **በክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ሲጸልዩ ለጸሎታቸው መልስ የሚመጣው ለምንድነው?**
   1. ሁሉም ኃይማኖቶች የሚጸልዩበት ህግ-መንገድ ወይም የጸሎት ሥርዓት አላቸው።
      1) ጸሎታቸውን ለእንስሳት ሲያቀርቡ ለምንድነው መልስ የሚያገኙት?
      2) ለድንጋይና ለዛፍ ጸሎት ሲያቀርቡ ጸሎታቸው መልስ የሚያገኘው ለምንድነው?
      3) ለሥዕል፣ ለፎቶግራፍና ለወረቀት ጸሎት ሲያቀርቡ ጸሎታቸው የሚመለሰው ለምንድነው?
      4) ለምንድነው ጸሎታቸውን ለሳጥንን በእጅ ለተሠሩ ጣዖቶች ሲያቀርቡ መልስ የሚያገኙት?
      5) አንዳንድ የኃይማኖት መሪዎች ሲጸልዩ ኃይል የሚያገኙት ለምንድነው? መልሱ የሚገኘው በ1ኛ ቆሮ 10፡20 እና በማቴ 24፡11 ላይ ነው።
   2. የማያምኑ ሰዎች ለጸሎታቸው መልስ ቶሎ ያገኛሉ። ነገር ግን መልካም ይሁን ክፉ መልስ ለሚፈልጉት ዓላማ ይገለገሉበታል። ነገር ግን በመጨረሻ ውድቀት ይመጣል።
   3. የእግዚአብሔር ልጆች ሲጸልዩ እግዚአብሔር በሦስት መንገድ መልስ ይሰጣል።
      1) አንዳንድ ጊዜ በሚጸልዩበት ጊዜ መልስ እንደጸሎታችን ወዲያውኑ ይሰጠናል።
      2) የማይጠቅመን ወይም የማያስፈልገን ሲሆን እግዚአብሔር ዝም ይላል።
      3) አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ከጸለይነው በላይ በሆነ መንገድ ይመልሳል። ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ሁልጊዜ ህዝቦቹን ሊባርክ ይፈልጋል።

2. **ከእግዚአብሔር መልስ መቀበል የሚችል ማን ነው ብቃት ያለው ማን ነው?**
   1. የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ መልስ ይቀበላሉ። (ዮሐ 1፡12)
   2. በኢየሱስ ስም ስንጸልይ (ዮሐ 16፡24)
   3. ኃጢአትን በመናዘዝ መልስን መቀበል (መዝ 66፡18)
   4. በእምነት ለሚጸልዩ እርሱ መልስ ይሰጣል (ሉቃ 11፡5-12)
   5. እስከ መጨረሻው ተግተው በትዕግሥት ለሚጸልዩ እርሱ መልስ ይሰጣል (ሉቃ 28፡1-8)

6. በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ መልስን ተቀበል በሀሳብህና በልብህ እርሱ ጥበብን ይሰጥሃል። (ፊል 4፡6-7)

3. **የእግዚአብሔር ልጆች ሲጸልዩ መጠንቀቅ ያለባቸው ነገሮች አሉ።**
   1. የእኔ ፈቃድ እንዲፈጸም ሳይሆን ትክክለኛው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም
   2. የእኔ ዕቅድ እንዲፈጸም ሳይሆን ነገር ግን ታላቁ የእግዚአብሔር ዕቅድ እንዲፈጸም
   3. የእኔ ሁኔታ ሳይሆን የእግዚአብሔር ድንቅ ዓላማ እንዲገለጽ
   4. በቂም በቀል ሕይወት ወይም ልብ ሳይሆን በይቅርታ ልብ በመሆን
   5. ራስን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በማስገዛት መንፈስ

4. **ጸሎት «መንፈሣዊ ምርምር» ነው**
   1. ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ይሠራል። (ሉቃ 11፡13፣ ማቴ 12፡28)
   2. መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ሲሠራ የክፉ መንፈስ ኃይል ይወድቃል። (ማቴ 12፡28-29)
   3. መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ሲሠራ የእግዚአብሔር መላዕክት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራት በኃይል ይንቀሳቀሳሉ።
      1) ዕብ 1፡14 2) ራዕ 8፡3-5 3) ዳን 10፡10-20
   4. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አከባቢህ መቀየር ይጀምራል። (መጽሐፈ አስቴር 4፡14)
   5. እግዚአብሔር የጸሎትህ መልስ የሚሆኑ ሰዎች ይልክልሃል። (ሐዋ 10፡1-9)
      1) ዘፍ 18፡2-15 (አብረሃም)
      2) 1 ነገ 19፡5-7 (ኤልያስ)
      3) 2 ነገ 6፡13-17 (ኤልሳ)
      4) 2 ነገ 20፡1-10 (ሕዝቅያስ)
      5) ሐዋ 1፡10-11
      6) ሐዋ 5፡19-20፣ 10፡1-4፣ 12፡1-10
      7) ራዕ 1፡1-20

ፈውስ - መድኃኒት የሌላቸው በሽታዎች፣ ካንሰር

1. የደህንነት ማረጋገጫ
2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ
3. የሰይጣን ሥራ
4. ፈውስ፡ የማያቋርጥ ቋሚ ጸሎት (በመንፈስ ቅዱስ መሞላት) እና አካላዊ ፈውስ
5. ትክክለኛ ምግብና መድኃኒት የእግዚአብሔር በረከቶች ናቸው።
6. ለመንፈሳዊ ችግሮች መፍትሄ መንፈሳዊ ኃይል አስፈላጊ ነው።

# 10

## ለምንድነው በሽታ በምንጸልይበት ጊዜ የሚለቀን?

ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት ጎራ ሲል የጴጥሮስ ዐማት በትኩሳት ታማ ተኝታ አገኛት። እጇን ዳሰሳት፣ ተኩሳቱም ለቀቃት ተነስታም አገለገለቻቸው። በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ እርሱ አመጡ፡ እርሱም መናፍስትን በቃሉ አስወጣ በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ። በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፡ «እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፣ ሕመማችንንመ ተሸከመ» (ማቴ 8፡14-17)

ኢየሱስ ወንጌልን ሰብኳል በተመሳሳይ ሁኔታ በሽተኞችን እንደፈወሰ። ሐዋሪያትና የቀደሙት የእምነት አባቶች ወንጌልና የፈውስ አገልግሎትን ጎን ለጎን አስኪደዋል። ኢየሱስ እርግጠኛ ተስፋ ሰጥቶናል። (ማር 16፡15-20)

1. **በመጽሐፍ ቅዱስ የፈውስ ቃል ኪዳን ተገብቶልናል።**
    1. የነኩትም ሁሉ ተፈወሱ (ማር 6፡56)
    2. እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፣ ሕመማችንንም ተሸከመ (ማቴ 8፡17)
    3. በመገረፉ ቁስል እኛ ተፈወስን (ኢሳ 53፡5)

2. **በመጀመሪያ ሥር ለሰደደው በሽታ መሰረታዊ ምክንያት የሆነውን ችግር ፈልግ/መርምር።**
    1. ባለመጠንቀቅ ብዛት፣ በብዙ ሥራ በመድከም ምክንያት፣በግድየለሽነት ምክንያት የሚፈጠሩ በሽታዎች አሉ።
    2. ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል እንደሚናገረው በሰው ሰራሽ መንገድ መዳን የማንችላቸው በሽታዎች አሉ። ከእነዚህ በሽታዎች ለመፈወስ መንፈሣዊ እርዳታ ያስፈልጋል።

        1)በኃጢአት ምክንያት የሚከሰት በሽታ
        - ሀ. የአባቶችና የቀደሙ አያቶች ኃጢአት
          በጣዖት አምልኮ ምክንያት ቅጣት እስከ ሶስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ
        - ለ. የወረስነው ኃጢአት
          ምክንያቱም መንፈሳችን በሞተ ሁኔታ ወስጥ ነው መፈወስ በማይችልበት ሁኔታ
        - ሐ. ዋና እውነተኛ ኃጢአት
          (2 ነገ 5፡7፣ 2ዜና 21፡12-19፣ 1ዜና 5፡5)

        2) ሰይጣን ያመጣው በሽታ (ክፉ መንፈስ ያመጣው)
        - ሀ. የአእምሮ (ማር 5፡3-15)
        - ለ. የስሜት (ኤፌ 4፡23-27)
        - ሐ. አከባቢያዊ (ማቴ 12፡22-28)
        - መ. የነርቭ ችግር (ማር 9፡17፣ ሉቃ 13፡16)

3. **ትክክለኛ ያልሆነ ህክምና ወደተባባሰ ሁኔታ ይመራል።**

1. በዘመናዊ ህክምና ወይም መድኃኒት ላይ ብቻ ያተኮረ ህክምና
2. ስጋዊ ፈውስ ውጤት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ህክምና
3. ጸሎት በኃይማኖታዊ መንገድ ላይ የተደገፈ፣ ጥንቆላ ክፉ መንፈስ

**4. ትክክለኛውን የፈውስ ሥርዓት እወቅ**

1. በመጀመሪያ መንፈሣዊ ፈውስ ያስፈልጋል (1 ዮሐ 1፡2)
    1) ኢየሱስ ክርስቶስን በልብህ ተቀበል (ዮሐ 1፡12)
    2) በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ (ኤፌ 5፡18)
2. ኃጢአትን መሥራትን አቁም (ያዕ 5፡13-16)
3. አከባቢህን ሁኔታህን አስተካክል (ማቴ 12፡25-29)
4. አሁን የታዘዘልህን መድኃኒት በአግባቡ ተጠቀም (ያዕ 5፡13-14)

**5. ከፈውስ በኋላ የምታደርገው ነገርም አስፈላጊ ነው።**

1. የእምነት ሥራህን ቀጥል።
2. የምስጋና ልብና ሕይወትህን ጠብቅ።
3. የምስክርነት ሕይወት ኑር።

- ፈውስ - ኤድስ
  1. ኤድስ የመጣበት ዘመን
  2. የጾታ ግራ መጋባትና ድንዛዜ ዘመን
  3. እንዴት አድርገን ልናክመው እንችላለን?
      1. ይህ በእውነት የማይፈወስ በሽታ ነው?
      2. በጸሎት ኃይል መፍትሄ አግኝ
      3. እግዚአብሔር በዚህ ምድር የምንፈወስበት ምግብ አዘጋጅቶልናል።
  4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው መፍትሄ መፈለግ ያለብን።